# ሠ ቅ ጸ ሊ

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን



የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ልዩ | ዕትም ፲፱ | ቀን: ሚያዚያ ፳፫ | በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ


## «የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች» እንዳይሆን እንሰጋለን!

የትግሬ-ወያኔ ጭምብል የሆነው ኢሕአዴግ አምጦ የወለደው አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ከሥልጣን መንበሩ በወጣ በ30 ቀኖች ውስጥ፣ የኦሮሞ ብሔርተኞች ላለፉት 70 ዓመታት' ዉሸቱን እውነት፣ ቅዠቱን ሕልም፣ ልብወለዱን ታሪክ፣ ፈጠራውን ነባራዊ ወዘተ አስመስለው የደከሙበትን የኦሮሞን ሕዝብ የመገንጠል፣ የኦሮሚኛን ቋንቋ ብሔራዊ የሥራ ቋንቋ የማድረግና ሠፊው የኢትዮጵያ ሀብት የያዘውን መካከለኛውን፣ ደቡብ ምዕራቡንና ምሥራቁን የኢትዮጵያን ክፍለ-ግዛቶች የአንድ ነገድ ብቸኛ ባለቤት የመሆን ምኞት የመጨረሻውን ይሁንታ ሰጥቷል። ማንም የኢትዮጵያን ፖለቲካ የሚከታተል ሰው ሊገነዘበው እንደሚችል፣ ዛሬ አገራችን ለገጠማት የመበታተን አደጋ፣ የቁልቁለት ጉዞውን ያስጀመራት የግራው ርዕዮት አራማጅ የሆነው (ግን ደግሞ ጎሰኝነትን በአፎቱ ደብቆ የያዘ) የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ እንደነበር ይገነዘባል።

ይህ ግራ ዘመም እንቅስቃሴ፣ ኢትዮጵያውያንን በጨቋኝ እና በተጨቋኝ መደቦች (ጨቋኝ ብሔር እና ተጨቋኝ ብሔረሰቦች) ብሎ በመክፈል፣ ለረጅም ዘመናት በአንድነት "ኢትዮጵያ የምትባል አገርና ኢትዮጵያዊ የተሰኘ ዜጋ" የፈጠሩትን ነገዶች አጥፊ አድርጎ በመሳልና የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በመክፈት ኢትዮጵያውያን ፊትና ጀርባ ከመሆን ዘለው፤ ይሄዉ በግራ ርዕዮት አፎት የተደበቀ ጎሰኝነት ሌላውን ኢትዮጵያዊ የተባለዉን ለማጥፋት በሚችለዉ መንገድ ሁሉ ሰይፉን ተጠቀመ። ይባስ ብሎም በቋንቋ ላይ በተመሠረተ አንድነት ጎራ ለዩ። በዚህ የጎራ ሰልፍ፣ የትግሬ-ወያኔ ዘረኛ ቡድን ከሸዕቢያ ጋር በፈጠረው አንድነት፣ የሌሎች ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ዐማራ ቡድኖች አውራ ሆኖ በመውጣት፣ እኒሁ ቡድኖችን በአምሳሉ ቀርፆ በማደራጀትና በመምራት በዐማራውና በአንድነት ኃይሉ ላይ ዘመቻ ከፈተ። ዘመቻው በግልጽ የተከፈተ 1972 ዓ.ም ጎሕ ሲቀድ ቢሆንም ይባስ ብሎ ደግሞ በሕጋዊ ሽፋን የተሰኘ ማንፌስቶ በመባል የሚታወቀውን፣ የሦስቱ ፀረ-ዐማራና ፀረ-ኢትዮጵያ ቡድኖች፣ ማለትም ሻዕቢያ፣ ሕወሓትና ኦነግ ለኤርትራ መገንጠልና ኢትዮጵያን ወደብ አልባ የሚያደርግና ቀሪው የኢትዮጵያ ክፍል በቋንቋ ልዩነትና ዐይን ባወጣ በመሬት ወረራ/ነጠቃና ላይ የተመሠረተ ፌዴራላዊ አስተዳደር እንዲመሠረት ተስማሙ።

በስምምነቱ መሠረት ኤርትራ ተገነጠለች። ኢትዮጵያም ታሪካዊ ወደቧን አሰብን አጣ ዝግ መሬት ሆነች። ኦነግ ወያኔን አንጋሽ በመሆኑ በምትኩ የአገሪቱን ዕምብርት እና የተፈጥሮ ሀብት ክምችት ባለቤት የሆኑትን ክፍለ ሀገሮች፣ «ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ» በሆነ መንገድ አዲስ «ኦሮሚያ» የሚል ሥያሜ ፈጥሮ ለራሱ ወሰደ። በዚህ የአገር ቅርምት ውስጥ ዐማራው በጠላትነት ተፈርጆ ከሠፊውና ከለሙ የአባቶቹ ክ/አገሮች እርስቱ ተገፍቶ፣ የበሬ ግንባር በሚያክል መሬት ላይ እንዲታጎር ፈረዱበት። በሠፊዋ ኢትዮጵያ እንዳይኖር ተከለከለ። ከግድያ በተዓምር የተረፈው፣ እየተወገዘና እየተዋረደ ተባረረ። ይህ

ድርጊት ኦነግ ውሸቱን እውነት አድርጎ ለአራት አሥርተ ዓመታት የጮኸለት የኦሮሚያ ምድር ከሕልምነት ወደ ገሐድነት ተለወጠ። ጥንትም ክልክል የሌለበት የኦሮሚኛ ቋንቋ አዲስ ልዩነት ለመፍጠር ላቲን ፊደላትን ከወደ አዉሮፓ አስመጥቶ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ተብዮ የሥራ ቋንቋ ሆነ። ይህም የልዩነቱን ግንብ በማስፋት፣ ልዩነቱ የበለጠ በነገዶቹ መካከል እስከ ወዲያኛው እንዲቀጥልና በሁለቱ ማለትም በዐማራና በኦሮሞ ነገዶች ፍቺ፣ የወያኔን የአገዛዝ ዕድሜ ለማራዘም እንዲቻል፣ የተስፋዬ ገብረዐብ "የቡርቃ ዝምታ" የሀሰት ድርሳን የወለደው «አኖሌ» የተሰኘ፣ « ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ» እንደሚባለው፣ የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ሠራዊት በአርሲ ሴቶች ላይ የፈጸሙት የጡት ቆረጣ ማሳያ የተባለ ሀውልት ተገነባ። ይህ ሀውልት ሁለቱ ነገዶች አጥፊና ጠፊ መሆናቸውን የሚያሳይ ቋሚ ምስክር ሆኖ እንዲታይ በመደረጉ ታሪኩንና ዕውነታውን የማያውቁ የኦሮሞ ልጆች በዐማራው ነገድ ላይ፣ ጥርስ ከመንከስ ዘለው፣ በቻሉትና ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በዐማራ ላይ ክንዳቸውን እንዲያነሱና ሰይፋቸዉን እንዲመዙ በማድረግ መጠነ ሠፊ የሆነ የዐማራ ሕዝብ በሐረርጌ፣ በአርሲ፣ በወለጋ፣ በኢሉባቡር፣ በከፋ ወዘተ በግፍ እንዲጨፈጨፍ ሆነ። የመጭው ትውልድም በሚያየው ሀውልት ቂም ቋጥሮ ዐማራን በጠላትነት ፈርጆ እንዲቆምና የሁለቱ ነገድ ልጆች በአጥፊና በጠፊነት እንዲቆሙ በወያኔ ታስቦና ተሰልቶ ተሠራ። የዚህ ሥራ ግብም ዐማራና ኦሮሞን ለያይቶ በማቆም የትግሬ-ወያኔን የአገዛዝ ዕድሜ ያላንዳች ተቀናቃኝ ለማራዘም መሆኑ ግልጽ ነው።

ይህ ዐማራና ኦሮሞን የማለያየቱ ጉዳይ፣ አናሳውና አገር አጥፊው በትግራይ ምድር ላይ የበቀለ ትውልድ ለ27 ዓመታት በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ተንሰራፍቶ እንዲቆይ ካስቻሉት ነገሮች ሁሉ ዋናው እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህን በተመለከተ ሟቹ መለስ ዜናዊ፣«ዐማራና ኦሮሞ ደግመው ኃብቻ ከፈቸሙ፣ ድርጅቴ ሕወሓት ማቅ ትለብሳለች፣ ያን ጊዜ ያልቅልናል» ከማለቱ ባሻገር የበታች ሹሞቹ እነ ገብሩ አሥራት ሳይቀር "የኦሮሞ ፖለቲካ ብሔርተኝነት ከሌለዉ ዋጋ የለዉም" እያሉ ብዙ ዐማራዎችን ከማስጨረስ አልፎ ተርፎ እስከ ወዲያኛዉ የትግሬ-ወያኔ ሕልውና መሠረቱ የሁለቱ ነገዶች መለያየትና መነጣጠል እንደሆነ ጉልህ ማሳያ ነው።

ይህን የተረዳው የዐማራ ሕዝብ፣ በተለይም በወልቃይት ጠገዴ የማንነት ጥያቄ ጥያቄ ዙሪያ ጎንደር ላይ የተፋፋመው የእንቢተኝነት እንቅስቃሴ፣ ያለፈውን በደል ለታሪክ በመተው፣ «ያለፈው ቅራና ነው፣ መጭው መጫኛ ነው» በሚለው ይትባህሉ፣ በፈጠራ ታሪክ በራሱ በዐማራ ላይ የተፈጸሙበትን ግፎች፣ ለአንድነትና ለሰላም ሲል «ይቅር» በማለት፣ «የኦሮሞው ደም ደማችን ነው!» የሚል መፈክር በማንሳት ባቀጣጠለው እልህና ቁጭት የተሞላበት ሕዝባዊ እንቢተኝነት፣ የሁለቱ ነገድ ፖለቲካኞች የከረረ አቋማቸውን ለጊዜውም ቢሆን እንዲያለዝቡ ማድረጉ አይዘነጋም።

ይህ የተካረረ አቋም መለዘብ ብቻ ሳይሆን፣ የሁለቱ ነገድ ሕዝብ ድምፅ ወደ ዋናው የጋራ ጠላታቸው ወደ ሆነው የትግሬ ወያኔ አገዛዝ ላይ እንዲያተኩር በማድረጉ፣ ወያኔ በአንድ ዓመት ውስጥ ሁለት ጊዜ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲያውጅ ከማስገደድ አልፎ፣ የትግሬ-ወያኔ ጭንብል የሆነውን የኢሕአዴግ እህት ድርጅቶች በመከፋፈል፣ የመራር ለውጥ እንዲያደርግ ማስገደዱን ተገንዝበናል። የአመራር ለውጡም ኃይለማርያም ደሣለኝ፣ በዐቢይ አሕመድ ጠቅላይ ሚኒስትርነት እንዲተካ አድርጓል። ነባሮቹ ሚኒስትሮች የቦታ ለውጥ እንዲያደርጉ ሆኗል። ይሁን እንጅ ይህ ለውጥ ሕዝብን ማዘናጊያ እና የትግሬ-ወያኔ የፈለገውን እንዲያደርግ የጊዜ መግዣ መሆኑን ሕዝባችን ከወዲሁ ሊረዳ ይገባል።

የትግሬ-ወያኔ አነሳሱ የትግራይ ረፑፐሊክ ለመመስረት ቢሆንም ቅሉ ወቅት የሰጠዉ ቅል ዱባ ይሰብር ነዉና በእርሱ የበላይነትና አድራጊ ፈጣሪነት የምትገዛ ኢትዮጵያ እስካለች ድረስ ለመቀጠልና፣ በሕዝብ ዕኩልነት፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ፣ ሰላም የሰፈነባት ኢትዮጵያን እንድትኖር እንደማይሻ ፕሮግራሙ እና ላለፉት 28 ዓመታት ያወጣቸው ፖሊሲዎች ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ። በኤርትራ መገንጠል፣ በኢትዮጵዮ ኤርትራ ጦርነት ድል ላይ የተፈጸው የአልጀርስ ስምምነት ሴራ፣ ከግብፅ ጋር ዐባይን በተመለከተ የገባው ውል፣ አገሪቱን በቋንቋ ሸንሽኖና የዐማራን የአባቶችን እርስት ወሮና በደንብር ይገባናል የፈሰሰው ደም፣ ከሁሉም በላይ አገሪቱን ያለወደብ ያስቀረበት ምክንያት ፣የትግሬ-ወያኔ ፀረ ዐማራ ብቻ ሳይሆን፣ ፀረ-ኢትዮጵያ መሆኑን ከሚያሳዩት ነቃሾች ጥቂቶቹ ናቸው።

የዚህን ያላለቀ ሴራ አደገኝነት ዛሬ የነበረውን እንዳልነበር የሚያደርግ የይዞታና የአካባቢ ግዛቶችንና የከተማዎችን ባለቤትነት የሚደነግጉ አዋጆችን የማውጣት ዘመቻን ይመለከታል። በተለይ ዐማራዉን በገጠሩም ይሁን ከከተማ ቦታዉ በማፈናቀል ላይ ያተኮሩ ተከታታይ ድርጊቶች የዚሁ እኩይ ድርጊት መገለጫዎች ናቸዉ:: በአብይ የሥልጣን ዘመን ያልተጠና፣ ከራሱ ሀሳብ ያልፈለቀ፤ የትግሬ-ወያኔ ዐማራና ኦሮሞው እንዳይገናኙ ፣ በጠላትነት እንዲቀጥሉ የሚያስችለውን

ሥልት አጥንቶ ያዘጋጀውን አዋጅ፣ አብይ ሥልጣን ተረከበ በተባለ በ30 ቀን ውስጥ የኦሮሞ ሕዝብ የአዲስ አበባ ልዩ ጥቅም ማስከበሪያ አዋጅ ፣ የኦሮሚኛ ቋንቋ የብሔራዊ ቋንቋ መሆን አዋጅ፣ የኢትዮጵያ አውራጃ፣ ወረዳ፣ ከተሞችና መንገዶች ስሞች በኦሮሞ ስሞች እንደሚለወጡ የሚያዝ አዋጅ እንዲወጣ ተደርጓል። የአዲስ አበባ መንገዶችና ሀውልቶችም ስም እንደሚለወጥ አዋጁ ያስገነዝባል።

እነዚህ አዋጆች የአብይን ፍላጎት ያንፀባርቃሉ ቢባል እንኳ፣ በራሱ የአገዛዝ ዘመን ተጀምረው የተፈጸሙ አለመሆናቸው አዋጆቹ የወጡበት ጊዜ ያሳያል። የአዋጆቹ ዋና ግብም ዐማራና ኦሮሞን ለመለያየት ተብሎ እንጅ በእዉነተኛ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የሚደረቱ ለዉጦች ሁነው አይደለም!። እንዲያዉም ወደ አንድነት እየመጣ ያለውን የሁለቱን ነገድ ልጆች በአዲስ ስልት መለያየት ነው። በነዚህ አዋጆች ኦሮሞቹ እሰይ! ፍላጎታችን ተሳካልን! ልጃችን ለመብትና ጥቅማችን ቆመልን! እንዲሉና በምናብ ዓለም እንዲዋኙ ማድረጉ እየተስተዋለ ነው። በኦሕዴድና በኦነግ መካከል የሥልት እንጂ፣ የዓላማ ልዩነት ስለሌለ፣ ኦነግ ያሰበው ተፈጸመ፣ ልጆቻችን ለኦሮሞነት የከፈሉት መስዋዕትነት ለፍሬ በቃ ብለው እንዲያምኑ ለጊዜውም ቢሆን፣ በድል አድራጊነት ስሜት ውስጥ እንዲገቡ ያደረገ እንደሆነ እየተስተዋለ ነው።

በሌላ በኩል ዐማራው የለም የአባቶቹን ምድር ልንነጠቅ አይገባም። ዛሬ ኦሮሚያ ተብሎ በተከለሉት ክፍለ-ሀገሮች ውስጥ የሚገኙ ከተሞችና አውራጃዎችን ስም ወደ ኦሮሞ ስሞች ይለወጡ ከተባለ፣ ስሞቹ መለወጥ ካለባቸው ከኦሮሞ(ጋላ) ወረራ በፊት ይጠሩ በነበረበት ስሞች መሆን አለበት የሚል ጭብጥ የያዘ፣ ሠፊ ታሪካዊ የሰነድ ማስረጃዎች ያሉት ክርክር ሊያነሱ ነው። አዋጁ እንደሚለው ዛሬ ያሉት የአውራጃ፣ የወረዳና ከተሞች ስሞች ወደ ኦሮሚኛ ስሞች የሚቀየሩ ከሆነ፣ የዐማራው ልጅ ደግሞ የለም፣ ይቀየር ካላችሁ በጥንት ስማቸው ይጠሩ ማለቱ ሳይታለም የተፈታ ነዉ። እንደ አብነትም የሚከተሉትን ሥራያሜዎች እንደሚከተለዉ ይዞ ይቀርባል!!

| ተራ ቁጥር | ነባር ስም | ከኦሮሞ ወረራ በኋላ የተሰጠ ስም | የሚገኙበት አካባቢ | ጥንታዊ ነዋሪ ነገዶች |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ቢዛሞ | ቄለም | ምዕራብ ወለጋ | ጋፋት፣ዐማራ፣ቤንሻንጉል፣አንፌሎ፣ሌሎች የጠፉ ነገዶች |
| 2 | ዳሞት | ሌቃ | ምሥራቅ ወለጋ | ጋፋት፣ ዐማራ፣ሌሎች የጠፉ ነገዶች፣ |
| 3 | እናርያ | ኢሉባቦር | ኢሉባቦር | ዐማራ፣ ከፍቾ፣ ሌሎች የጠፉ ነገዶች፣ |
| 4 | ገሙ | ጂማ | ጂማ | የም(ጃንጀሮ) ገሙ፣ዳውሮ፣(ኩሎ) ሌሎች የጠፉ ነገዶች |
| 5 | ገንዘ | ጅባትና ሜጫ | ምዕራብ ሸዋ | ጋፋት፣ ዐማራ፣ሌሎች የጠፉ ነገዶች፣ |
| 6 | ግራሪያ | ሰላሌ | ሰሜን ሸዋ | ጋፋት፣ ዐማራ፣ሌሎች የጠፉ ነገዶች፣ |
| 7 | እንደጥና | እንጦጦ፣ ጉለሌ፣ የካ | አዲስ አበባ ዙሪያ | ሜያ፣ዐማራ፣ ሌሎች የጠፉ ነገዶች |
| 8 | በረራ | ፊንፊኔ | አዲስ አበባ | ሜያ፣ዐማራ፣ ሌሎች የጠፉ ነገዶች |
| 9 | አ(ወ)ይጃ | የረርና ከረዩ | ምሥራቅ ሸዋ | ሜያ፣ ሐዲያ፣ ከንባታ፣ሲዳማ፣ሌሎች የጠፉ |
| 10 | ፈጠጋር | አርሲ | አርሲ | ሐዲያ፣ ከምባታ፣ሜያ፣ዐማራ፣ አዳል(አፋር)፣ ሲዳማ፣ሌሎች |
| 11 | ደዋሮ | ጭሮ | ምዕራብ ሐረርጌ | ሐዲያ፣ ከምባታ፣ ዐማራ፣ ሌሎች |
| 12 | ላኮመልዛ | ወሎ | ደቡብ ወሎ | ዐማራ፣ አዳል(አፋር)፣አገው፣ ሌሎች |
| 13 | ቤተ-ጊዮርጊስ | ወረኢሉ | ወረኢሉ | ዐማራ፣ |
| 14 | ቤተ-ዐማራ | ወረሂመኖ | ወረሂመኖ | ዐማራ |
| 15 | አንጎት | ራያ | ሰሜን ወሎ | ዐማራ፣አፈው፣አዳል(አፋር) |
| 16 | ባሊ | ባሌ | ባሌ | ሐዲያ፣ ከምባታ፣ሜያ፣ ዐማራ፣ ሲዳማ፣ ሌሎች |

የዐማራው ነገድ፣ ታሪክን የሚመለከተው የማንነቱ ማኅተም፣ መገለጫ፣ የዛሬና የነገ መሠረትና የወደፊት መስፈንጠሪያ ቦርድ ሆኖ በሚያገለግል መልኩ ነው። ታሪክ በቦታና በጊዜ ላይ የተመረኮዘ ኩነት ዉጤት ከመሆኑ አኳያ ለወደፊት ጉዞ እርሾ፣ ካለፉ ስህተቶች መማሪያ፣ የወደፊት ጉዞ መስተዋት እንጂ፣ የዛሬውን ማፍረሻ አይደለም።

ዛሬ የትግሬ-ወያኔ ኢትዮጵያን የማፍረሻ፣ የዐማራና የኦሮሞ ነገዶች መናቆሪያ እንዲሆን ተዘጋጅቶ፣ በኦሕዴዱ አፍላ የጫጉላ የሥልጣን ሙሽራ ወቅት የታወጀው፣ የአውራጃ፣ የወረዳ፣ የከተሞች፣ የመንገዶችና መሰል ስሞች በኦሮሚኛ ስማቸው ይጠራሉ ማለት፣ ታሪክን አለማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ አገርና ትውልድ ማፍረሻ፣ የትግሬ-ወያኔ አገር መበታተኛ ዕቅድ መሆኑን ማጤን ብልኅነት ነው እንላለን። ወደ ሠፊውና ረጅሙ ታሪካችን ከገባን፣ ስሞቹ የነማን፣ ነዋሪዎቹ እነማን እንደሆኑ እጅግ ብዙ የሆኑ ዘመን ጠገብ መረጃዎች ያሉ ስለሆነ፣ እነዚያን ወደኋላ ተመልሶ ማንሳቱ የሚጎዳው ማንን እንደሆነ ሊጤን ይገባል። ወደዚያ ከገባን «የቆጡን አወርድ ባል፣ የብብቷን ጣለች» እንዳይሆን ቀናዉንና ለጋራ የሚበጀዉን ጎዳና መምረጡ ዐዋቂነት ነዉ!! ክርክሩ ከቦታ ስም ለውጥ አልፎ የናንተ አይደለም፣ የእነገሌ ነው ወደሚል ሊለወጥ እንደሚችል መገንዘብ ተገቢ ነው። ኦሕዴድና የኦሮሞ ፖለቲከኞች ብልኅ ከሆኑ፣ ከወያኔ ወጥመድ ወጥተው፣ ነባሩ አንድነታችን የበለጠ የሚጠነክርበትን መንገድ ቢከተሉ፣ የኦሮሞ ሕዝብ ከስሙ ይልቅ የጋራና ሰፊዉ ኢትዮጵያዊ ማንነታቸው/ን ይልቃል። የሕዝቡ ቁሣዊ ጥቅም የሚከበረው በስሞች ለውጥ ሳይሆን፣ በአገር ባለቤትነቱ ነው። አገር ስንልም ወያኔ ከልሎ የሰጠው በረት ሳይሆን፣ በሠፊዋ ኢትዮጵያ ተዘዋውሮ መሥራትና መኖር ሲችል ነው። የሥራው ውጤት ብቸኛው ተጠቃሚነቱ፣ የዜግነት መብቱ መረጋገጥ ነው። በያዘው ላይ የሚጨምርለት እንጂ፣ የያዘውን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ፣ አጠቃላይ የአገር ጥፋትን እንጂ፣ ተጠቃሚነትን አያረጋግጥም። ይህ አረጋጋጭ ቢሆን ኖሮ፣ አገሪቱና ሕዝቡ ዛሬ ለገቡበት መቀራቅር ዉስጥ ባልገቡ ነበር። የለም የታገልነው ለስም ለውጥ ነው ከተባለ፣ ባንድ ወቅት ዶ/ር መረራ ጉዲና እንዳሉት "የኦነግ ትግል ደብረዘይትን ቢሾፍቱ፣ ናዝሬትን አዳማ፣ አዲስ አበባን ፊንፊኔ ከማለት ያለፈ ሊሆን አይችልም" ያሉት ዕውነት መሆኑን ያሳይል። ይህ ደግሞ ለማናችንም ጥፋትን እንጂ፣ ልማትን አያስገኝም።

የለም! ጥንትም በጉልበታችን ይዘናል፣ ዛሬም በዚያው መንገድ እንቀጥላለን!፣ ያውም የሁለቱም ጠላት በሆነው የወያኔ ሤራ ማስፈጸሚያነት እንቀጥላለን ከተባለ፣ መከራ የበዛበት የዐማራ ልጅ፤ «የማን ቤት ጠፍቶ የማን ይበጂ፣ የአውሬ መውለጃ ይሆናል እንጂ!» በሚል ቁጭት የተያያዘውን ትግል በማጠናከር የታሪካችን አንዱና ሠፊው አካል በሆነው የመጠፋፋት አዟሪት ውስጥ ሳይወድ ተገዶ የሚገባ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) የዐማራው ወጣት ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርገውን፣ ያለፉት ታሪኮቻችን የወደፊት ጉዞአችን መስፈጠሪያ፣ የትውልድ ተከታታይነት ማሳያ፣ የነባር ሕዝብነት መገለጫ በሚሆን መልኩ ማንም ከማንም ሳያንስ፣ ሁሉም በችሎታው ተወዳድሮ የፈለገውን መሆን የሚችልበት ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆን ከመጣር ጎን ለጎን፣ የአባቶቻችን ታሪክና መልካም ስም ለማጥፋት የሚደረገውን ዘመቻ ለመመከት ወደ ኋላ የማይል መሆኑን ወዳጅና ጠላት አስቀድመው እንዲያውቁት እንሻለን።

ይህም በመሆኑ፣ የአውራጃ፣ የወረዳና የከተሞችን ስምለ ለመለወጥ ሙከራ ከተደረገ፣ ኢትዮጵያዊነትን ከመስበክ በተጓዳኝ፣ ዘመን ጠገብ የሆኑ የታሪክ ነቃሾችንና እና ዋቢዎችን መነሻና መድረሻ በማድረግ፣ የአገሪቱ ልዩ ልዩ ስሞች ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው፣ ከኦሮሞ ወረራ በፊት በነበሩት ስሞች እንዲጠሩ ዘመቻ ለመክፈት እንገደዳለን። አገሩ የኦሮሞዎች ብቻ ሳይሆን፣ የዐማራው፣ የሚያው፣ የአንፈሎው፣ የሐዲያው፣ የከንባታው፣ የጉዳጌው፣ የአገው፣ የአፉሩ፣ ወዘተ ስለሆነ በአንድ የኦሮሞ ስም ሊተካ አይገባውም የሚል የጠነከረ ተቃውሞ በማቀንቀን፣ ባለህ እርጋ ከሚል የወል አቋም ሕዝብችን እንዲደርስ አበክረን ልንተጋ ይገባል።

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው@!